

በ: ኤሪክ ሊትዊን
ምሳሌዎች: ጀምስ ዲን
ተርጓሚ: כנרת
የእድሜ ክልል: ታዳጊዎች

קְרִיאָה

እንደገና" - ምክር ለቤተሰባዊ ንባብ"

ታዳጊዎች ብዙውን ጊዜ ተመሳሳይ ታሪክ እንዲነበብላቸው ይጠይቃሉ – ለእነርሱም የሚጠቅመውን ነገር ያውቃሉ! ዳግመኛ ማንበብ ታዳጊዎች አስደሳች ተሞክሮዎችን እንዲያሳድጉ፣ ወደ ስሜቶችና ውስጣዊ ፍላጎቶች በጥልቀት እንዲመረምሩ፣ ከሚያውቋቸው ክፍሎች ጋር እንዲቀላቀሉና ቃላትን በመደጋገም እንዲማሩ ያስችላቸዋል።

שִׂיחָה

የማበረታቻ መዝሙር

ሻኡል እየሄደ እያለ መራመድ ምን ያህል እንደሚወድ የሚያበረታታና የሚያስታውስ ዘፈንና ይዘምራል። ታዳጊዎቹን፡- ‘‘ማበረታቻ መቼ ነው የፈለጋችሁት?’’፣ የራስዎን አዲስ የማበረታቻ ዓረፍተ ነገር ወይም በሻኡል ግጥም ላይ የተመሰረተ ዓረፍተ ነገርን አንድ ላይ (ለምሣሌ፡- ‘‘ወደ መናፈሻ ቦታ መሄድና ሁሉንም ጓደኞቼን ማግኘት እወዳለሁ’’ በማለት መጠየቅ ይችላሉ። በዓረፍተ ነገሩ ላይ ዜማ ማከልም ይችላሉ።

סִרְטוֹנִים

QR ኮድ

የሚያበረታቱ የመንገድ ዘፈኖችን ይወዳሉ? ኮዱን ስካን ያድርጉና በይግአል ባሻን፣ ዑዚ ሂትማንና ዮናታን ሚለር የተጫወቱትን “ሆፓ ሃይ” የሚለውን የተለመደ ዘፈን ያዳምጡ።



מִשְׂחָק

በተለያዩ ጫማዎች መራመድ

በቤተሰብ ውስጥ ላሉ ወንድና ሴት ልጆች ጫማ – የቤት ለቤት ጫማ፣ ነጠላ ጫማ፣ ቡትስ ጫማና ሌሎችም – በተለያየ መጠን፣ ዓይነትና ቁሳቁስ ማምጣት የሚችሉ ሲሆን ታዳጊዎች በእነርሱ ውስጥ እንዲራመዱና በተለያዩ ጫማዎች መካከል ያለውን የልዩነት ስሜት እንዲሰማቸው መጋበዝ ይችላሉ።



חֵקֶר

በመታጠቢያ ገንዳ ውስጥ ማክበር

የሻኡል ጫማ ወደ ገንዳው ውስጥ ሲገባ እንደገና ነጭ ይሆናል! ገንዳውን በሳሙናና በውሃ ሞልተው የቆሸሹ ጫማዎችን ወይም አሻንጉሊቶችን በመውሰድ በመታጠቢያ ገንዳው ውስጥ አስገብተው ማጠብና ቀለሙ እንዴት እንደሚቀየር ማየት ትችላላችሁ።





ፒንተረስት

መዝሙሮች፣ ስራዎችና ሌሎች አስገራሚ ነገሮች በፒጃማ ቤተ መፃህፍት ፒንተረስት ላይ ይጠብቁዎታል።